# ከእግዚአብሔር ፍቅር

" … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

**ሐምሌ** 1996 **July** 2004 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)

www.ethioGodslove.org አዘጋጅ :- መላኩ ማሞ ትዕዛዙ


## ከግብረ ሥጋ ሱስ ነፃ መውጣት

ግብረ ሥጋ (sex) በትዳር ለተጣመሩ ወንድና ሴት ብቻ የተፈቀደ የፍቅርና የመዋለጃ ተግባር ነው። በዚህም መልክ ቅዱስና ክቡር ነው። ስለ ሆነም በጥንቃቄ መጠበቅ ይኖርበታል። መጽሐፍ እንዲህ ይላል "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር <u>መኝታውም ንፁሕ ይሁን፤</u> ሴሰኞዎችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።" (ዕብራውያን 13÷4)

የግብረ ሥጋ ሱስ፡- አዘውትሮ ስለ እርሱ በማሰላሰል÷ በምዕራቡ ዓለም ገበያ የሚገኙትን ሥዕሎች (pornography) በማየት÷ ወደ አመንዝሮች በመግባት÷ የዋሕ ሰዎችን ከትዳር ውጭ በማማገጥ ወዘተ ምርኮኛውን ያጠምዳል። በዚህ ሱስ የተጠመደ ሰው÷ሰውን የሚመለከተው በሴሰኛ ዓይኖች ብቻ ስለ ሆነ ፍቅር አይኖረውም። በትዳሩም ርካታ÷ሰላምና ጽናት የለውም።

የሚከተሉት ከግብረ ሥጋ ሱሰኛነት ለመገላገል የሚረዱ የጥናት ውጤት የሆኑ ምክሮች ናቸው። A way of Escape: Freedom from sexual strongholds ከተባለ መጽሐፍ ተወስዶ ተዘጋጀ።

☑ ከተቃራኒ ፆታ ጋር ወዳጅነትህ በግብረ ሥጋ ፍላጎት ላይ ሳይሆን በፍቅር ላይ የተመሠረተ ይሁን። እግዚአብሔር ግብረ ሥጋን የፈቀደው÷ተፋቅረው ቃል ኪዳን የተጋቡ ሰዎች ፍቅራቸውን እንዲገላለጹበትና እንዲራቡበት ብቻ መሆኑን ተረዳ። <u>ግብረ ሥጋ የፍቅርና የቃል ኪዳን የመጨረሻ ደረጃ ነው።</u>

☑ በዚህ ሱስ የተጠመድህበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ እንዲገልጽልህ ጌታን ጠይቀው። ጤነኛ ያልሆነ የግብረ ሥጋ አመለካከት ያሳደረብህ÷ ያሳለፍኸው ልምምድ ቢኖር÷መንፈስ ቅዱስ እንዲያስታውስህ ጸልይ። በዚህ ጠንቅ ለመጠመድህ ምክንያት የሆነህ ሰው ከታወሰህ በይቅርታ ማረውና ተፈታ።

☑ ጌታ ክርስቶስ እየሱስ ከማንኛውም ክፉ ነገር ሊፈውስህ ችሎታም ፍላጎትም እንዳለው ዕመን። እርሱም በሞቱና በትንሣዔው÷ የኃጢአትን ኃይል አስቀድሞ የሰበረ መሆኑን አስታውስ። ሙታንን እንኳ ማስነሣት የቻለውን ኃይሉን ዛሬ በሕይወትህ እንድትለማመድ ይወድዳል።

☑ እስከ ዛሬ ያደረግኸውን ማንኛውንም የግብረ ሥጋ ኃጢአት ተናዘዝ። ከዚያም እያንዳንዱን በስሙ እየጠራህ በመጸየፍ÷ በጌታ ፊት ንስሐ ግባ። ከዝያም በኋላ ጌታ ጸጋውን እንዳበዛልህ መጠን፡- ከዚህ ነገር ንጽሕናህን ጠብቀህ ለመኖር ለጌታ ቃል ግባ።

"… ወንድሞች ሆይ÷ ሰውነታችሁን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ÷ …" ተብሎ በሮሜ 12÷1 እንደ ተጻፈው፡- ሰውነትህን ከኃጢአት አርቀህ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ደስ በሚለው ንጽሕና ለመጠበቅ ወስን። ግብረ ሥጋን ከቃል ኪዳን የትዳር ጓደኛህ ብቻ ጋር ለማድረግ በጌታ ፊት በዕውነት ቃል ግባ።

☑ ባለትዳር ካልሆንህ፡-እስከ ትዳር ድረስ በንጽሕና ለመኖር የሚያስችልህን ጸጋ እንዲያበዛልህ በጾምና ጸሎት ተደገፍ። ምክንያቱም ንፅሕና (ቅድስና) ያለ ጾምና ጸሎት አዳጋች ስለ ሆነ ነው።ጌታ ግን በንጽሕና መኖራችንን እጅግ ስለሚወድ ርዳታው ለሚሹት ሁሌ ዝግጁ ነው ጌታ ይመስገን።

☑ ዓይኖችህ ይጠንቀቁ!! ልብህንም ጠብቅ!! ለምሳሌ በቴሌቪዥን ወይም በተግባረ ሥጋ ሥዕሎች የታየ ነገር ለብዙ ዓመታት በአእምሮ ተቀርጾ መርዝና ፈተና ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የምታየውን÷ የምታሰላስለውንና የምትውልባቸውን ቦታዎች በጥንቃቄ ምረጥ። ጌታ መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አእምሮህን እንዲያድስልህ ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስህን እያጠናህ የምትጸልይበት ቋሚ ጊዜ ይኑርህ። በዚህ አኳኋን ጌታ ታላቅ ፈውስን ብቻ ሳይሆን÷ ክብሩንም ያጎናጽፍሃል።

☑ ደግ የእግዚአብሔር ሰው፡-ችግርህን ተረድቶ የሚደግፍህ ወዳጅ (ሞግዚት ደጋፊ÷አማካሪ) ይኑርህ። የቤተ ክርስቲያንህ መጋቢ (ቄስ) ወይም በቃሉ ዕውቀትና በሕይወት የበሰለ÷ማንኛውም ታማኝ ክርስቲያን ለዚህ ብቁ ነው። አንተም ለሚረዱህ ሰዎችና ለእግዚአብሔር ዕውነተኛ ሁን። ከሁሉም ይልቅ እርሱ የማያውቀው ነገር ስለ ሌለ ÷ በጌታ ፊት ግልጽና ዕውነተኛ ሁን፡

☑ የተበላሸን ሕይወት ማስተካከል ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም÷ጌታ ግን በእርሱ ታምነህ በምታልፍበት ሁኔታ ሁሉ ሊረዳህ÷ እስከ መጨረሻው ÷ ከአንተ ጋር መሆኑን በፍጹም አትዘንጋ።

☑ እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን የማይለዋወጥ ፍቅሩን አምነህ ተቀበል። የግብረ ሥጋ ኃጢአት አብዛኛውን ጊዜ ባለመወደድና በኵነኔ ስሜት ይሞላል። ሆኖም ከልብ ተጸጽተህ÷ንስሐ ገብተህ÷ ለመተው ከወሰንህ፡- የልጁ የእየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ሊያነፃህ በቂና ዝግጁ ነው።

☑ የቀረው ዘመንህ ብሩክና ጤነኛ እንዲሆንልህ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ከቋሚ የጸሎት ሕይወት ፈቀቅ አትበል፡

"… ጽና÷እጅግ በርታ፤ባርያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ (የመጽሐፍ ቅዱስህን ቃል) ጠብቅ÷አድርገውም፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ÷ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም፡ በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና÷አይዞህ፤ …" (መጽሐፈ ኢያሱ 1÷7-9)

## የመልስ ወራት

ውድ አንባቢዎቻችን፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን። በዩናይትድ ስቴትስና በካናዳ÷ እንዲሁም በአውሮፓ÷በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ፡- መልዕክታችን የሰራጫል። እየሰፋም ነው። የዌብ ገጽ አገልግሎታችንንም የሚጠቀሙ ወገኖች ቁጥር እየበዛ ነው። ለምሳሌ በዚህ ዓመት በመጋቢት ወር 441 ጊዜ ÷ በሚያዝያ ወር 532 ጊዜ÷ በግንቦት ወር ደግሞ 520 ጊዜ ሰዎች ከመላው ዓለም የዌብ ገጻችንን ጎብኝተዋል።

ጥሪአችን የጌታ እየሱስ ክርስቶስን ቤት በቃሉ በማጽናናትና ሌሎችም እንዲጨመሩ እየጋበዝን መገለጡን መጠባበቅ ነው። ከመልዕክታችን ይዘትና አቀራረብ ይህን መረዳት ይቻላል። ጌታ መንፈስ ቅዱስ በመራን አርዕስት በኪስ የሚያዝና በቶሎ ለማንበብ የሚመች አቀራረብ÷የመረጥነው ሆን ብለን ነው። በቃላት ብዛት ወይም በሰው ዕውቀት ሳንታመን የቃሉና የመንፈሱ ወቅታዊ አሸንዳ ለመሆን ራሳችንን ማቅረባችን ነው።

በዚህ ደረጃ ሥርጭት ከጀመርን አራተኛ ዓመታችን ነው። አሁን ግን ቆም ብለን÷ ይህን በየወሩ ወጪውን ችለን የምንልክላችሁን የደብዳቤ አገልግሎት ማስተዋል አለብን። ለዚሁም÷ቢቻል ከሁሉም አንባቢዎቻችን መስማት እንሻለን። ስለዚህ ሁላችሁም፡- ከሚቀጥለው ወር ማለቅ በፊት፡- እንድትጽፉልን በትሕትና እንጠይቃችኋለን። ጥያቄአችን ይህ ነው፡-

### ይህ ደብዳቤ ምን ያህል ጠቃሚ ነው?

የምትተባበሩን ሁሉ ጌታ እየሱስ አብዝቶ ይባርካችሁ።

እየሱስ ጌታ ነው። ጌታ ይባርክህ።

www.ethioGodslove.org


አድራሻችን፡-

GOD'S LOVE
P.O.BOX 6734
LEE'S SUMMIT, MO 64064,
USA

hello@ethiogodslove.org

# የሥዕል ጨረታ

በዩናይትድ ስቴትስ በጣም ሐብታም የሆኑ አባትና ልጅ ነበሩ። እነርሱም በዓለም ላይ ብርቅ የሆኑትን የታዋቂ ሠዓሊዎችን  ሥዕል ገዝተው ያጠራቀሙ ነበር። ፒካሶ ከተባለው ጀምሮ ሩፋኤል  እስከ ተባለው ታዋቂ ሠዓሊ ድረስ የሁሉንም ሰብስበዋል። አንዳንዴ አባትና ልጅ አብረው ተቀምጠው በሰበሰቡአቸው ሥዕሎች አሠራር ይደነቁ ነበር።   የሥዕሎቹም ግምት ብዙ ሚሊዮን ዶላር ነበር።

የቬየትናሙ ጦርነት በተጀመረበት ጊዜ ልጅየው ወደ ጦርነት ግዳጅ መሄድ ነበረበት።ልጁም እጅግ ጀግና ስለ ነበረ  በጦርነት  ሜዳ  ጓደኛው ቀስሎ  ከወደቀበት  አንስቶ ሲያሸሽ በድንገት በጥዪት በተመታ ጊዜ ወዲያው ሞተ።  ወዲያውም  መርዶው ለአባትየው ደረሰ። አንድ ልጁ ስለ ነበረ፥እጅግ አምርሮ አለቀሰና አዘነ።

አንድ ወር ያህል አለፈ። የልደታ በዓል ከመድረሱ ሳምንት ያህል ሲቀረው፥ አንድ ቀን የአባትየው በር ተንኳኳ። በሩንም ሲከፍቱ ትልቅ ጥቀልል በእጁ የያዘ ወጣት በበሩ ቆሟል። ያም ወጣት የአክብሮት ሰላምታውን ካቀረበ በኋላ ራሱን እንዲህ ሲል ማስተዋወቅ ጀመረ።

“የወዳጄ አባት ሆይ÷እኔ እርስዎን አላውቅም ነበር፡፡   ነገር ግን ልጅዎ እኔን ለማዳን ነበር ነፍሱን የሰዋው፡፡ በጦር ሜዳ ቆስዬ ልሞት ሳለሁ እኔን ለማዳን ተሸክሞ ሲያሸሸኝ  ተመትቶ ሞተ፡፡  ዛሬ ሕያው ሆኜ በፊትዎ መቆም የቻልሁት በልጅዎ ሞት ምክንያት ነው፡፡  ወደ ጦርነት ከመሄዳችን በፊት የሥዕል አድናቂነትዎን አዘውትሮ ይነግረኝ ነበር” በማለት በእጆቹ የያዘውን ስጦታ አቀበለ፡፡  “ይህ ስጦታዬ  እጅግ አነስተኛ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ራሴ የሣልሁት ነው፡፡ ታላቅ ሠዓሊም አይደለሁም፡፡ ሆኖም ልጅዎ ይህን ሥዕል ቢቀበሉኝ ደስ የሚለው ይመስለኛል፡” አለ፡፡

አባትየውም  የስጦታውን ጥቅልል ተቀብሎ ከፈተው።  ከሞት የተረፈው ወጣት ራሱ  የሣለው የልጁ  ምሥል ነበር። ወጣቱም በሚያስደንቅ አኳኋን የልጁን ባሕሪይ በሥዕል ማስፈሩ የሚያስገርም ስለ ነበረ አባትየው  እጅግ ተደነቀ። እምባም ተናነቀው።ወጣቱንም  አመሰገነና  ዋጋውን  ሊከፍለው ለመነው። ወጣቱም፡- ልጅዎ ያደረገለኝን  በዋጋ  መክፈል  ስለማይቻል፥ የምሥጋና ስጦታዬን ይቀበሉ አለ።

አባትየውም ሥዕሉን ወስዶ በግድግዳው  ላይ  ሰቀለው።  ማንኛውም ጎብኚ ወደ ቤቱ ሲመጣ በታዋቂ ሰዓሊዎች የተሣሉትን ሥዕሎች  ከማሳየቱ አስቀድሞ የልጁን ሥዕል ያስጎበኝ ነበር።

ከዚያም ብዙም ሳይቆይ ሰውየው አረፉ። በዚህም ምክንያት የሰውየውውድ የሥዕል ስብስብ በጨረታ መሸጥ ነበረበት። የሥዕሎቹንም ዋጋ የተረዱ በርካታ ሐብታሞችና የአካባቢው ክቡራን ተሰበሰቡ።ሁሉም አንዱን እንኳ ለመግዛት ቢችሉ ይመኙ ነበር።

በጨረታው  መድረክ ላይ  የልጁ ሥዕል ተቀምጦ ነበር። ከዚያም የጨረታው መሪ  ጨረታውን  ለመጀመር ምልክት ሰጠና “ጨረታው የሚጀምረው  በልጁ ሥዕል ነው።  የሚፈልግ ሰው ዋጋውን መናገር ይጀምር” በማለት ጨረታውን ከፈተ።

ሕዝቡም  ፀጥ  አሉ።  አንድም ሰው የልጁን ሥዕል መግዛት አልፈቀደም። ከዚያም ከወደ ጥጉ ከቆሙት አንዱ “የታወቁ ሠዓሊዎች የሣሉትን ነው የምንፈልገው፥ የልጁን አንፈልግም” ሲል ጮኸ።

ነገር ግን ባለ ጨረታው ተስፋ ሳይቆርጥ መነዝነዙን ቀጠለ።  “የልጁን ሥዕል የሚገዛ አንድም ሰው አይገኝም? መቶ ዶላር፥ ሁለት መቶ ዶላር” እያለ መገፋፋቱን ቀጠለ።

ደግሞ ሌላ የቁጣ ድምፅ “የመጣነው የፒካሶን  ሥዕል  ብለን ስለ ሆነ የልጁን ነገር  ተወውና ዕውነተኛውን ሥዕል አቀርብልን” ሲል ጮኸ።

አጫራቹ ግን ምንም ሳይበገር ልጁን! ልጁን! እረ ልጁን ተቀበሉ!  ማን ነው ልጁን የሚቀበል?  እያለ  መነዝነዙን አላቋርጥ አለ። ብዙም ታገሰ።

በመጨረሻ፥በመግቢያው ጥግ ራቅ ብለው  ከተቀመጡት  መሐል አንድ ድምፅ ተሰማ።  እርሱም ቀደም የልጁና የአባትየው  አትክልተኛ  የነበረ ሰው ነው።  እርሱም  “አሥር ዶላር እከፍላለሁ” ሲል ፍላጎቱን አስታወቀ፡ ድኃ  ስለ ነበረ  ያለውን  ሁሉ  ነው የሰጠው።

ባለጨረታውም ተጽናንቶ “አሥር ዶላር አግኝተናል፤ ጨምሮ መውሰድ የሚፈልግ አለ”?   በማለት ቢጠይቅ ማንም ስላልቀረበ፥ አሥር ዶላር ለከፈለው ለመስጠት ወሰነ።

በሥፍራው የተሰበሰቡት ቁጣቸው ነደደ። ሁሉም የልጁን ነገር አልፈለጉም። “የከበረውንና ታዋቂውን” ብቻ መግዛት ይፈልጉ ስለ ነበረ ነው።

በጨረታው ማጠቃለያ  ባለጨረታው አንድ፥ ሁለት፥ ሦስት፥ ጨረታው በአሥር ዶላር ተሸጦአል በማለት አበቃ በዚህም ጊዜ፡-በመጀመሪያው ረድፍ ከተሰለፉት ሐብታሞች  አንዱ  ይህ ያልተፈለገ ሥዕል በመሸጡ ደስ አለውና “በሉ እንግዲህ ወደ  ዕውነተኞቹ ሥዕሎች እንለፍ!” ሲል  ጮኸ።

ከዚያም ባለጨረታው የጨረታውን ምልክት አስቀመጠና “በጣም አዝናለሁ።  ጨረታው አብቅቷል።”  ሲል አስታወቀ።

ሕዝቡም  “ይህ እንዴት ይሆናል? የቀሩትስ  ሥዕሎች ምን  ይሆናሉ?” በማለት በቁጣ ጠየቁ።

የጨረታውም  መሪ  ሲመልስ፡- በጣም ይቅርታ፥  ይህንን ጨረታ ለማካሄድ በተጠራሁ ጊዜ፡-  መግለጽ ያልተፈቀደ  ሚስጢር በኑዛዜው ውስጥ ነበረ። ሚስጢሩም ለጨረታ የሚቀርበው  የልጁ  ሥዕል ብቻ መሆኑ ነው።  ያም ብቻ ሳይሆን፡-  የልጁን ሥዕል  የገዛ  ሰው፡-  ሌሎቹን ሁሉ የመውረስ መብት ይሰጠዋል።   ልጁ ያለው  ሁሉን  ያገኛል። ሲል ደመደመ።

አያችሁ፡- እግዚአብሔር ከሁለት ሺ ዓመታት ገደማ በፊት  በመስቀል ላይ አሳልፎ ልጁን ሰጥቷል፡፡  ሰዎች ተቀብለው  ይድኑበት ዘንድ÷ እንደ ባለጨረታው፡-ልጁን! ልጁን! ልጁን! ልጁን ተቀበሉ! ከክፉ መንገዳችሁም ተመለሱ!  የሚለው ድምፅ  አሁንም በዓለም ዙሪያ ያስተጋባል፡፡    ልጁን የሚያገኝ መልካሙን ሁሉ ይወርሳል ከአሁንና ከሚመጣው  አይጎድልበትም፤ የሚለው ድምፅ  አሁንም ያስተጋባል፡፡



ምክንያቱም

“በእርሱ የሚያምን ሁሉ  የዘላለም  ሕይወት  እንዲኖረው እንጂ  እንዳይጠፋ  እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን  እስኪሰጥ ድረስ  ዓለሙን  እንዲሁ ወዶአልና፡፡”
(የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

ወገኔ ሆይ፡- እስከ ዛሬ ስንት ጊዜ  ስለ ልጁ ስለ እየሱስ ክርስቶስ  ሰምተሃል? መጽሐፍ ቅዱሳችን  በ1ኛ ዮሐንስ 2÷23፡- “ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን (ግን) አብ ደግሞ አለው፡፡” ይላል፡፡ እንዲሁም  በዚሁ መጽሐፍ  በምዕራፍ 3 “ኃጢአትን የሚያደርግ  ከዲያብሎስ ነው÷ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና፡፡ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ (ጌታ እየሱስ) ተገለጠ፡፡ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም÷ ዘሩ በእርሱ  ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም  ተወልዶአልና፡ ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር ልጆችና  የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ  ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡”
(1ኛ ዮሐንስ 3÷ 8-10)

## አንተ ከእግዚአብሔር ነህ? አዎን ካልህ፡- ርግጠኛ ነህ? አንቺስ?

ከእግዚአብሔር መሆን እንዲህ ይጀመራል፡፡

### የንስሐ ፀሎት

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡- ኃጢአተኛ መሆኔን አምናለሁ፡፡ ልጅህ እየሱስ  የሞተው  ለእኔ  መሆኑን አምናለሁ፡፡  ከክፉ መንገዴ እመለሳለሁ፡፡ እየሱስ ሆይ! ጌታና አዳኜ መሆንህን  አምኜ  እቀበላለሁ፡፡ ስለዚህ  ወደ መንግሥትህ ተቀበለኝ፡፡  አስተምረኝም፡፡  አሜን፡፡

## እየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡